# ሞለፈፈው፣ ላጠው!

የሰው ነገር ጉድ…
ጤና መስሎ ዕብድ!
ሁለት ዱርየዎች ጥል የጠማቸው
እየተራገጡ በእግር ጫማቸው
እየተጯጯኹ ወርደው ቁልቁለቱን
ከተፍ አሉብን ስንይዝ ዳገቱን

አወይ ጥጋባቸው…
ማን ተዉ ሊላቸው!
እንደ ደረሱብን ካጠገባችን
ተጋፍተው ገቡብን ከመሃላችን
አሳዳጁ ደርሶ አንገቱን ሲያንቀው
ያኛው ኡኡታውን ጮኸት ለቀቀው!

ምን እንዳጣላቸው
ምን ዐውቀንላቸው!
ከማንም አውታታ፣ ዱርዬ መሃል
ማን ደፍሮ ይናገር? ማን ይገላግል?
የተጣሉበትን መች ይናገራሉ፣
በእርግጫ፣ በጡጫ ይነራረታሉ!

አንዱ ያየለው
ከመሬት ጣለው!
ይዞ እንደ ድንች እያገላበጠው
ከመ-ቅጽበት ልብሱን ሞለፈፈው፣ ላጠው
ከዚያም ረግጦ፣ ረግጦ እያወላገደ
ከጭቃ ለውሶት፣ ገፍፎት፣ ጥሎት ሄደ።

እግዚኦ መሐረነ
ቅድስት ስሓሊለነ!
የደካማን ጥቃት ጠባቂ የሚያይ
ፖሊስ ወዴት ሄደ፣ ዳኛ የለም ወይ?
ከንቱ የሰው ምኞት ከፀሐይ ለመድረስ
ከጭቃ ተፈጥሮ ጭቃ ለሚመለስ

ገ/ኢ. ጐርፉ።